# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| | | |
|---|---|---|
| 1kki Diro Kiiro 6<br>Hawassa, Ella 29, 2012 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Amaale Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፮<br>ሀዋሳ ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም |


## Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Xaphoomu Seeru Allaalshi Loosu Mini Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawi Kiiro 6/2012

Itophiyu Federalitte Dimokiraasitte Rippaablike Mootimma giddo tonnikki qoqqowo ikke tantanamino Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bayriidi Seeranna Bayriidi Seeri amanyoote hattono seeru aliidimma ayirrisiisanno Xaphoomu Seeru Allaalshi Loosu Mini biilloonyenna loosu qeecha mura hasiissinota ammannoonnihura;

Babbaxxitino seeru allaalshi loosu qeechuwa mitteenni qineessine islancho, guma afidhinno owaate uyitannonna dagoomunna mootimmate horo wo’millunni agarsiisannonna seera ayirrisiisanno kaajjado seeru allaalshi loosu mini looso hanafanno gede assate

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤትን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፮/፳፻፲፪

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት አስረኛ ክልል ሆኖ ለተቋቋመዉ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስቱን እና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን እንዲሁም የህግ የበላይነትን የሚያስከብር የዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ስልጣን እና ተግባር መደንገግ እንደሚገባ በመታመኑ፤

የተለያዩ የዓቃቤ ህግ ተግባራትን በአንድ ላይ በማቀናጀት ጥራት ያለውና ተደራሽ የሆነ ውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጥ፤ የሕዝብንና የመንግስትን ጥቅም በተሟላ ሁኔታ የሚያስጠብቅ አንድ ጠንካራ ሕግ አስከባሪ የዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ወደ ስራ ለማስገባት ስልጣን እና ተግባር መወሰን አስፈላጊ ሆኖ

biilloonyenna loosu qeecha mura hasiisse leeltinohura;

Dagoomu ammanamooshshi noosihanna wo'ma uurrinshate wolaphonni owaatanno hattono ogimmasira, uurrinshatenna dagate xa'mamooshshinni galannoha, yawosi xawo ikkinonna dagate beeqqooshshe buuxisino garinni loosanno Xaphoomu Seeru Allaalshi Loosu Mini biilloonyenna loosu qeecha gumula hassiissinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Qoqqowu Bayriidi Seera quwa 48 cinaancho quwa 3 (a) aana uynoonni biilloonyi garinni aaninoha lallamboonni.

## GAFA MITE

## XAPHOOMU WORO

**1. Harancho Birxicho**

Konne lallawa "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Xaphoomu Seeru Allaalshi Loosu Mini Biilloonyenna Loosu Qeecha Murate Fulino Lallawa Kiiro 6/2012" yine woshshinara dandiinanni.

**2. Qaallate Tiro**

Ho'rosi garinni wole tiro uynanniha ikka hoogiro konni lallawi giddo፡

1. **"Qoqqowo"** yaa Sidaamu Dagoomu

በመገኘቱ፤

የሕዝብ ተአማኒነት ያለው በተሟላ ተቋማዊና ሙያዊ ነፃነት የሚያገለግል እንዲሁም ለሙያዊ፣ ተቋማዊና ሕዝባዊ ተጠያቂነት የሚገዛ፣ በግልጽነትና በአሳታፊነት የሚሰራ የዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ስልጣን እና ተግባር መወሰን በማስፈለጉ፤

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ሀ ላይ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 6/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር፤

1. **"ክልል"** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ

Qoqqowooti.

2. **“Amaalete Mine”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma seera fushanno bisooti.
3. “**Jeefisiisaanote Amaale Mine”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma aliidi looso gumulsiisanno bisooti.”
4. “**Qoqqowu Mootimma Loosu Minna”** yaa seerunnni mannima noosiha ikke wo’munni wo’ma woy gamunni mootimmate baajeettenni galtanno bisubbaati.
5. **“Seera”** yaa Federealete mootimmanni fulte qoqqowu giddo jeefisantanno seerubbanna qoqqowu giddo seera fushshate roorre noonsa bisubbanni fulanno lallawa, wodhonna biddissaati.
6. **“Baayriidi Seera”** yaa Itophiyu Federaalitte Dimokiraasitte Rippaabilike Mootimmanna /woy Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Baayriidi Seeraati.
7. **“Jaddote Seera”** yaa Itophiyu Federaalitte Dimokiraasitte Rippaabilike Dagate Riqiwaano Amaale Mininna Qoqqowu Mootimma

ነዉ፡፡

2. **“ምክር ቤት”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት የህግ አዉጭ አካል ነው፡፡
3. **“የመስተዳድር ምክር ቤት”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚ አካል ነው፡፡
4. **“የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች”** ማለት ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በክልሉ መንግስት በጀት የሚተዳደሩ አካላት ማለት ነዉ፡፡
5. **“ሕግ”** ማለት በፌደራል መንግስቱ ህግ አውጪ ወጥተው በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት ያላቸው የሕግ ማእቀፎችን፣ በክልሉ ሕግ አውጪ አካላት የወጡ አዋጆችን ደንቦችን እና ስልጣን በተሰጣቸው የክልሉ መንግስት አካላት የወጡ መመሪያዎችን ያጠቃልላል፡፡
6. **“ሕገ-መንግስት”** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና/ወይም የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ሕገ-መንግስትን ያጠቃልላል፡፡
7. **“የወንጀል ሕግ”** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተደነገገ

babbaxxitino hajo aana fushshitinno jaddote worooti.

8. **“Biilto”** yaa qoqqowu mootima loosu mine woy mootimmate lophote uurrinshubba giddo biiloonsinoonniha, qoqqowu amaale mini miila woy woradu amaale mini woy quchumu amaale mini miila ikke dagatenni doorantino woy duuchunku deerrira heeranno aye biili woy dagate tantanoto giddo sooreessimmatenni woy boordete miilimmanni woy massagaanchimmatenni biiloo’me woy somame woy doorame loosanno mancho yaate.

9. **“Biila”** yaa qoqqowoho, zoonete, woradaho, quchumu gashshootiranna oolluu deerrira seerunni woy hajote ledo xaadooshshu noose galtinote wodhonni qoqqowu mootimma loosu mine woy mootimmate loosu uurrinshara woy dagate uurrinshuwa giddo biiloo’me woy doorame woy somame loosanno mancho yaate.

10. **“Muishshu Jaddo”** yaa 1997 M.D fulino Federaalete Mootimma Jaddote Seera, Federaalete Muishshu Jaddo Lallawi Kiiro 881/2007 hattono woloota muishshu jaddo yine murroonnireeti.

የወንጀል ሕግ እና በክልሉ መንግስት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የወጡ የወንጀል ድንጋጌዎች ናቸዉ፡፡

8. **“ባለሥልጣን”** ማለት በክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅት ውስጥ የተሾመ፣ የክልሉ ምክር ቤት አባል ወይም የወረዳ ወይም የከተማ ምክር ቤት አባል በመሆን በህዝብ የተመረጠ ወይም በሁሉም ደረጃ ላይ ያለ ማንኛውም ተሿሚ ወይም በህዝባዊ አደረጃጀቶች ውስጥ በኃላፊነት ወይም በቦርድ አባልነት ወይም በአመራርነት ተሹሞ ወይም ተመድቦ ወይም ተመርጦ የሚሠራ ሰው ማለት ነው:::

9. **“ተሿሚ”** ማለት በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደርና ቀበሌ ደረጃ በህግ ወይም አግባብነት ባለው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ተሹሞ ወይም ተመርጦ ወይም ተመድቦ የሚሠራ ማለት ነው፡፡

10. **“የሙስና ወንጀል”** ማለት በ1997 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የወንጀል ህግ፣ በፌዴራል የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 እና በሌሎች

11. **"Taakisete Jaddo"** yaa jaddote seera woy Taakisete seera sae gabbarotenna takisete aana loonsoonni jaddooti.

12. **"Loosunna Mannoomu Agarooshshenna Woowe**" yaa jaddo loosamase kulanno woy naqqasanno woy maatensa aana jaddo loosamase kulansa woy naqqasansa korkaatinni mannoominsa aana illitanno gawajjo woy iillitansara mixi'noonni loosu woy loosu base soorro woy gaamooshshu woy aye loosu gawajjonni agaramate yaate.

13. **"Loosu Mine"** yaa Xaphoomu Seeru Allaalshi Loosu Mineeti.

14. **"Gahshootu Lophote Uurrinsha"** yaa qoqqowu mootimma wo'muni wo'ma woy gama annimmate qooda afidhino mootimmate lophote uurrinshaati woy Aksiyoneeti.

15. **"Qara Xaphoomu Seeru Allaalaancho"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaantichi shiqisheenna Qoqqowu Amaale Mine biloonsinanni Xaphoomu Seeru Allaalshi Loosu Mini albisaancho sooreessaati.

ህጎች የሙስና ወንጀል ተብሎ የተደነገገ ማለት ነው::

11. **"የታክስ ወንጀል"** ማለት የወንጀል ሕግን ወይም የታክስ ሕጎችን በመተላለፍ በግብር እና ታክስ ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ተግባራት ማለት ነው::

12. **"የሥራና የአካል ጥበቃ ዋስትና"** ማለት ጠቋሚዎችን ወይም ምስክሮችን ወይም ቤተሰቦቻቸውን ጥቆማ በመስጠታቸው ወይም በመመስከራቸው ምክንያት ከሚቃጣባቸው ወይም ከሚደርስባቸው የአካል ጉዳት ወይም ለመፈፀም ከታቀደ ወይም ከሚፈፀምባቸው የሥራ ዝውውር ወይም ምደባ ወይም ከየትኛውም የሥራ ጉዳት መከላከል ማለት ነዉ፡፡

13. **"መስሪያ ቤት"** ማለት የክልል መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ነው፡፡

14. **"የመንግሥት የልማት ድርጅት"** ማለት የክልሉ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የባለቤትነት ድርሻ ያለው የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም አክሲዮን ማኅበር ማለት ነው::

15. **"ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ"** ማለት ሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት በርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት በክልል ምክር ቤት የተሾመ የክልል ጠቅላይ

16. **“Layinki Xaphoomu Seeru Allaalaancho”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaantichinni motoo’mino Xaphphoomu Seeru Allaalshi Loosu Mini Layinki sooreessaati.

17. **“Seeru Allaalaancho”** yaa seeru ogimmanni owaante aara konni lallawinna seeru allaalaano galtinote wodho garinni mootoonsinoonni seeru ogeessa ikke Qaranna Layinki Xaphoomu Seeru Allaalaanonna hattono taqu taqunkunni heeranno seeru allaashi loosu mini sooreeyyeno hanqafanno.

18. **“Poolise”** yaa roorre noonsa qoqqowu woy federaalete poliseeti.

19. **“Mancho”** yaa kalaqamu woy seerunni mannimmate afamooshshe afirino bisooti.

## 3. Koo-teemmate Xawishsha

Konni lallawi giddo mitte koo-teemmanni worroonnihu horosi garinni wole koo-teemmano hanqafannoho.

ዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ነው፤

16. **“ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ”** ማለት በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር የተሾመ የክልል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ምክትል ኃላፊ ነው፤

17. **“ዓቃቤ ሕግ”** ማለት በዓቃቤ ህግ ሙያ እንዲያገለግል በዚህ አዋጅና በዓቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የተሾመ የህግ ባለሙያ ሆኖ ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉን፣ ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን እና በየእርከኑ ያሉት የዓቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ኃላፊዎችንም ይጨምራል፤

18. **“ፖሊስ”** ማለት ስልጣን ያለው የክልል ወይም የፌደራል ፖሊስ ነው።

19. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

## 3. የፆታ አገላለፅ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

## GAFA LAME

## HEXXO, GALTINOTE GARA, BIILLOONYENNA LOOSU QEECHA

**4. Hexxo**

Qoqqowu Seeru Allaalshi Loosu Minira aantete worroonni hexxo heedhannosi.

1. Bayriidi Seeranna Bayriidi Seeri amanyoote ayirrisanna ayirrisiisa;
2. Seeru aliidimma buuxanno;
3. Jaddote seera ayirrisiisa;
4. Qoqqowu mootimmanna daga fitaaberete horo ayirrisiisa.

5. **Qara Loosu Mini Borro Mine**

Qoqqowu Xaphoomu Seeru Allaalshi Loosu Mini Hawaasi quchumiraati.

6. **Galtinote Gara**

1. Xaphoomu Seeru Allaalshi Qoqqowu Prezidaantichinna Jeefisiisaanote Amaale Mini hundaanni galanno.
2. Taqu taqunkunni biiloonsinoonni Seeru Allaalshi

## ክፍል ሁለት

## ዓላማ፣ ተጠሪነት፣ሥልጣን እና ተግባር

**4. ዓላማ**

የክልሉ "ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መ/ቤት" የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖረዋል፡-

1. ሕገ-መንግሥቱን እና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማክበርና ማስከበር፤
2. የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፤
3. የወንጀል ሕግ ማስከበር፤
4. የክልሉ መንግሥት እና የህዝብ የፍትሐብሔር ጥቅም ማስከበር

5. **ዋና መስሪያ ቤት**

የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት በሀዋሳ ከተማ ይሆናል::

6. **ተጠሪነት**

1. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለመስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል።
2. በየእርከኑ የሚሾሙ የዓቃቤ ህግ

loosu mini sooreeyye deerru deerrunkunni heeranno qaru gashshaanchi woy kantiibichi woroonni galtanno.

3. Xaphoomu Seeru Allaalshi aye deerrira heedhanno seeru allaalaano aliidi sooreessaati.

4. Konni quwira cinaancho quwa 3 aana worroonnihu noo gedeenni heereenna aye deerrira noo seeru allaalaano gamaantino loosu handaari soreeyye woroonni galtanno.

7. **Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Loosu Mini aantete noo biilloonyinna loosu qeechi heerannosi.

1. Bayriidi Seeranna Bayriidi Seeri amanyoote ayirrisatenna ayirrisiisate hattono seeru aliidimma buuxantanno gede assanno; la’annonsa bisubba ledo loossanno.

2. Seeru hajo aana qoqqowu mootimma qara amaalaancho woy riqiwaancho ikke loosanno.

3. Federaalete mootimma jaddote farco polise qoqqowu giddo loosu aana hossanno gede qineessanno; harunsannonna buuxanno.

መምሪያ ሀላፊዎች ተጠሪነታቸው እንደ ቅድም ተከተላቸዉ በየእርከኑ ለሚገኙ ዋና አስተዳዳሪ ወይም ከንቲባ ይሆናል፡፡

3. በክልሉ በየትኛውም ደረጃ ለሚገኝ ዓቃቤያነ ሕግ የበላይ ኃላፊ ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ-ህግ ነው፡፡

4. በዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በየትኛውም ደረጃ ያለ ዓቃቤ ህግ ለተመደቡበት የስራ ዘርፍ ኃላፊዎቻቸው ተጠሪ ይሆናሉ፡፡

7. **ሥልጣንና ተግባራት**

መስሪያ ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ሕገ-መንግሥታዊና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲከበር እና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፡፡

2. በሕግ ጉዳዮች የክልል መንግስት ዋና አማካሪ እና ተወካይ ሆኖ ይሰራል፡፡

3. በፌደራል መንግስት የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡

4. Jaddote farco mashalaqqe gamba assanno, qineessanno, buunxanni amanyoote diriirsanno; jeefisanno.

5. Bayriidi Seerinninna wolu seerinni agarooshshe assinoonni qaansichunnita dammate qoossonna wolapho ayirrase buuxanno.

6. Qoqqowu jeefisiisaanote bisi biilloonyenna loosu qeecha murranni lallawi giddo jeefisiisaanote amaale mini miilla ikkitanno addinnina gutunni uyinoonni loosu qeecha loosu aana hosiisanno.

7. Qoqqowu jeefisiisaanote bisubba loosu minna loosu qeechansa seeru garinni loosansa buuxanno.

8. Qoqqowu yoote minnna roorreenyi hundaanni ubbanno muishu gargarooshshinna taakisete seera sa”atenni loosantanno jaddonna hattono jawanna xurqa ikkitino woloota jaddote assoote poolisete ledo halammetenni qorto assanno, aliidimmatenni massaganno.

9. Jaddote seerinna wolootu seerubba giddo murroonni muishu jaddo woy wole jaddo loosamase qummeessi iillisiro woy ikkado huluullo heedhusiro poolisete ledo halammetenni mashalaqqe gamba assanno; gamba assinanni

4. የወንጀል ፍትሕ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት መተንተንና ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈፅማል፡፡

5. በሕገ-መንግሥትና በሕግ ጥበቃ ያገኙ የዜጎች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል፡፡

6. የክልሉ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር በሚወስነው አዋጅ የመስተዳድር ምክር ቤት አባል ለሆኑ አስፈፃሚ አካል መስሪያ ቤቶች የተሠጡ የወል ሥልጣንና ተግባርን ሥራ ላይ ያውላል፡፡

7. የክልሉ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ተግባራቸውን በህግ መሠረት ማከናወናቸውን ያረጋግጣል፡፡

8. በክልሉ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር በሚወድቁ የፀረ-ሙስና እና የታክስ ህጎችን በመጣስ በሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች እንዲሁም ከባድና ውስብስብ በሆኑ ሌሎች የወንጀል ድርጊቶች የወንጀል ምርመራ ከፖሊስ ጋር አብሮ ያጣራል፣ ምርመራውን በበላይነት ይመራል፡፡

9. በወንጀል ህግ ወይም በሌሎች ህጎች ውስጥ የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ወይም የወንጀል ድርጊቶች ጋር በተያያዘ

gede assanno; hasiissanno gumulo aanno; uyinanni gede assanno.

10. Muishu jaddonni afi’noonni horo woy lexxo mootimmate higganno gede assanno; qolsiisanno; yekkeeramanno, ragisiisanno.

11. Muishu jaddoni shiqqino qaxxarro woy qortote harinsho aana noo muishu jaddo qaxxarote yekkeero gobbaanni gooffanno gede assanno; jeefinsanni gara wodhotenni murranni.

12. Jawa muishu jaddo qorto ledo amadame Jaddote Qorchi Amanyooti Seeri woy xaado afidhino wole seerubba garinni aye manchi heeranno mini, hoowe, woy loosu base woy aye jiro hasiise leelliro hedeweelcho fonqolchinsanni assanno; ha’runsanno, amadamanno woy seeru caali hundaanni galanno gede assanno.

13. Jaddote Qorichi Amanyooti Seerinna Muishu Gargarooshshi Baxxino Amanyooti Seeri garinni muishunni huluullammoonni manni 48 sa’’aate sa’inokki yannara yoote mini hajajo hasiissukkinni amadatenni poolisete xaawira keeshshitanno hajajo aanno.

ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ያለው እንደሆነ ከፖሊስ ጋር መረጃ ወይም ጥቆማ ይሰበስባል፤ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፤ ያሰጣል።

10. በሙስና ወንጀል የተገኘ ጥቅም ወይም ትርፍ ወደ መንግስት እንዲመለስ ያደርጋል፤ ይከሳል፤ ይከራከራል፤ ያስመልሳል፤ ያስወርሳል።

11. በሙስና ወንጀል የቀረበ ክስ ወይም በምርመራ ሂደት ላይ ያሉ የሙስና ወንጀሎች ከክስ ክርክር ውጭ እንዲያልቁ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙ በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

12. ከከባድ የሙስና ወንጀሎች ምርመራ ጋር በተያያዘ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ወይም አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች መሠረት የማንኛውንም ሰው ቅጥር ግቢ ወይም መኖሪያ ቤት ወይም የሥራ ቦታ ወይም ማንኛውንም ሀብት እንደ አስፈላጊነቱ እንዲበረበር ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ በቁጥጥር ሥር እንዲውል ያደርጋል።

13. በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግና በፀረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ህግ መሠረት በሙስና የተጠረጠሩ ሰዎችን የፍርድ ቤት ትዕዛዝ

14. Qortote assate hasiisannoha ikkiro Jaddote Qorichi Amanyooti Seerinna xaado afidhino wole seerubba garinni aye manchono woshshe woy shiqishiishe xa’manno; qaalesi ha’nanni gede assanno; aye manchiwiinni woy loosu mininni naqqaso shiqqanno gede hajajanno; shiqqino naqqasono haaranno.

15. Muishu woy Taakisete jaddonna afi’noonni woxe woy jiro huluullammanni manchi woy maatesi woy wolu manchi su’minni baankete noota woy akisiyoonete qoodi noosita ikkado huluullo woy naqqaso heedhuro Qara Xaphoomu Seeru Allaalaanchi hajajonni taje gamba assinanni gede assanno; hasiise leelliro yoote mini hajajonni woxisi woy jirosi milli yitannokki gede assanno.

16. Muishu jaddo assootinni afi’noonni woy kalaqi’noonni jiro woy iillitino gawajjo ledo amadante qortote aana noo aye manchi jiro yoote mini hajajonni ki’antanno gede assanno; jaddote loosinni afi’noonni woy daggino jiro ikkase buuxaanturo yoote mini hajajonni ragirantanno gede assanno.

ሳያስፈልግ ከ48 ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ በቁጥጥር ሥር በማዋል በፖሊስ ጣቢያ እንዲቆዩ ትእዛዝ ይሰጣል፡፡

14. ለምርመራ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች መሠረት ማንኛውንም ሰው አስቀርቦ ይጠይቃል፤ ቃሉ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ ከማንኛውም ሰው ወይም መሥሪያ ቤት ማስረጃ እንዲቀርብለት ያዛል፤ የቀረበለትን ማስረጃ ይወስዳል፡፡

15. ከሙስና ወይም ከታክስ ወንጀል ጋር በተያያዘ የተገኘ ገንዘብ ወይም ሀብት በተጠርጣሪው ወይም በቤተሰቡ ወይም በሌላ ሰው ስም በባንክ መኖሩ፣ የአክሲዮን ድርሻ እንዳለው በቂ ጥርጣሬ ወይም ማስረጃ ካለ በዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ትዕዛዝ ማስረጃ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ገንዘቡ ወይም ሀብቱ እንዳይንቀሣቀስ ያደርጋል፡፡

16. በሙስና ወንጀል ድርጊት የተገኘ ወይም የተፈራ ወይም ከደረሰ ጉዳት ግምት ጋር በተያያዘ በምርመራ ላይ ያሉ የማንኛውም ሰው ሀብትን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲታገድ ያደርጋል፤ የማንኛውም ሰው ሀብት በሙስና ወንጀል የተገኘ መሆኑ ወይም የተፈራ

17. Jaddotenni qaxxarama hoogate qoosso noonsarinna muishu jaddonna huluullammoonni woy qaxxarama noonsa mannootiti tini qoosso ka’anno gede roorreenya afirino bisira shiqishanno; fajjiniro poolisete ledo qorto assanno; qaxxaro shiqishanno; yekkeeramanno; jeefishshano harunsanno.

18. Muishu jaddo aanna beeqqino manchi hajo yoote mine shiqase albaanni hasiisannonna guma afidhino taje uyiro qaxxaramannokki gede assanno.

19. Dagate horo kaiminni woy jaddotenni xa’misiissannokki ikkito heerase xawo ikkite leelturo jaddote qorto uurritanno woy uurritino jaddote qorto suffanno gede assanno.

20. Aye jaddote qorto seeru garinni loosamase buuxanno; seeru fajjanno garinni hasiissanno hajajo la’annosi bisira aanno;

21. Qorto poolisetenni hanafantino mereerima, shotanna miicamaanchu hojji ku’lattonni shiqqanno jaddote hajubba qorto garunni buuxamase muli harunso assanno.

መሆኑ ከተረጋገጠ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሀብቱ እንዲወረስ ያደርጋል፡፡

17. በወንጀል ያለመከሰስ መብት ያላቸውና በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ወይም መከሰስ ያለባቸው ሰዎች ይህ መብት እንዲነሣ መብቱን ለማንሣት ሥልጣን ላለው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድ ከፖሊስ ጋር ይመረምራል፤ ይከሳል፤ ይከራከራል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

18. በሙስና ወንጀል ላይ የተካፈለ ሰው ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት አስፈላጊና ውጤታማ የሆነ መረጃ ከሰጠ ከክስ ነፃ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

19. በሕዝብ ጥቅም መነሻ ወይም በወንጀል የማያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠው የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡

20. ማናቸውም የወንጀል ምርመራዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤ አስፈላጊውን ህጋዊ ትእዛዝ ለሚመለከተዉ አካል ይሰጣል፡፡

21. ምርመራቸዉ በፖሊስ በተጀመረባቸው መካከለኛ፣ ቀላል እና በግል አቤቱታ በሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ምርመራ በአግባቡ ስለመከናወኑ በቅርበት ክትትል

22. Mootimmate loosu minna woy mootimmate lophote uurrinshuwa loosaasinenni woy biiltonsanni woy wolu manninni jaddo muishu loosamase qummeessi iillisiro woy ikkado huluullo heedhusiha ikkiro poolisete ledo qorto buxanno, buuxisiisanno; hasiissanno qaafo adhanno; adhinanni gede assanno;

23. Qoqqowu mootimmate uurrinshubbanna latishshu uurrinshubba eanno sheemati seeru garinni ikkasi qorqortanno, seeru amaalenna kaa'lo uytanno; Jeefishsha lainohunni jeefisiisaanote amaale mini wodho fushanno.

24. Jaddote taje aana seeru allaalaanchi woy yoote mini uyino gumulo hajo la'annose poolisete bisira egensiisanno.

25. Jaddote qorto tajubba lainohunni deerru deerrunni afantanno seeru allaalaano uyitino gumulo aana poolise shiqishshanno ku'latto lae gumulo aanno.

26. Qorto gundoonni tajubba Jaddote Amanyooti Seeri garinni worroonni bikkaasinchuwa

ያደርጋል።

22.በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሰራተኞች ወይም በባለሥልጣኖቻቸው ወይም በሌሎች ሰዎች የሙስና ወንጀል መፈፀሙን ጥቆማ ሲደርሰው ወይም በቂ ጥርጣሬ ያለው እንደሆን ከፖሊስ ጋር ይመረምራል፤ እንዲመረመር ያደርጋል፤ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል።

23.የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች የሚያደርጉትን ስምምነት በተመለከተ ሕጋዊነትን የመረምራል፣ የሕግ ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙ የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

24.በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠ የዓቃቤ ሕግና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከተው ፖሊስ ያሳውቃል፣

25.የወንጀል ምርመራ መዝገቦችን አስመልክቶ በየደረጃው ባሉ ዓቃቤያነ ሕግ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በፖሊስ የሚቀርቡ አቤቱታ ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል።

26.የተጠናቀቁ የምርመራ መዝገቦችን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ህግ መሰረት የተቀመጡ መመዘኛዎች

wo’mituro “diqaxxarsiissanno” woy “taje cufantino” yitanno gumulo aanno.

27. Seerunni bande fajjinoonni hajo aana hunaanchimmate torbo assanno; gumulanno; doorshu tirote qaafo adhinanni gede gumulanno; gumulo loosu aana hosaseno ha’runsanno.

28. Mootimma riqiwe jaddote hajo aana qaxxaro safanno, yekkeeramanno, dagate horora hassiisannoka ikke leelliro qaxxaro kayisanno, ka’ino qaxxaro suffanno gede assanno.

29. Jaddote assooti qummeessaanonna naqaashshe seeru garinni agarooshshe woy woowe afidhanno gede assanno.

30. Seeru seejjamaano woy poolisete mine woy seejjote mini giddo amadante woy usurante noo manni qoosso raguni agaramase harunsanno, qoossote agarama ikkitonna keeshshitanno yanna seeru garinni ikkasena hoogase buuxanno.

31. Araarunni gooffara dandiitanno jaddote assootuwa araarunni gooffanno doogo injeessanno.

ሲሚሉ የ‹አያስከስስም’ ወይም የ‹ተዘግቷል’ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

27. የህግ ተለይቶ በተፈቀዱ ጉዳዮች ላይ ጥፋተኝነት ድርድር ያደርጋል፤ ይወስናል፤ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ይወስናል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

28. መንግስትን በመወከል የወንጀል ጉዳዮች ክስ ይመሰረታል፣ ይከራከራል፣ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክስ ያነሳል፣ የተነሳ ክስ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡

29. የወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች በህግ መሰረት ጥበቃና ከለላ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

30. የህግ ታራሚዎች ወይም በፖሊስ ጣቢያ ወይም በማረሚያ ቤት ውስጥ በቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎች መብት መከበሩን ይከታተላል፤ የመብት አያያዝ ሁኔታ፣ የቆይታ ጊዜ በህግ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

31. በዕርቅ ሊያልቁ የሚችሉ የወንጀል ድርጊቶች በእርቅ የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

32. Yoote Minna jaddote hajo aana uyitanno gumulonna hajajo jeefamasenna ayirrase ha’runsanno.

33. Yoote minna sayissanno jadote qorichuwa garunni jeefantanno gede assate dandiisiisanno amuraate qineessanno woy qinaawasi buuxanno.

34. Reewote qorichi gumulo Federaalete Xaphoomu Seeru Allaalaanchi widoonni Itophiyu Federaalitte Dimokiraasitte Rippaabilike Pireezidaantichira shiqanno gede assanno; jeefishshano ha’runsanno.

35. Qoqqowu mootimmate loosu minnara dagatenna qoqqowu mootimma qoossonna horo riqiwe yekkeeramanno, agarsiisanno, agarantanno gede assanno, agarantanno harinsho ha’runsanno, qorqorsanno.

36. Qoqqowu mootimma riqiwatenni fitaabeerete qaxxaro safanno; Hasiishshu deerrinni uurrinshuwa riqiwe addinni woy mittimma yekkeeramannno.

37. Qoqqowu mootimma loosu minna mimmitinsa ledoo sumuu yitinokkinna hojji uurrinshuwa woy hojji manchi ledo kalaqantanno fitaabeerete

32.ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ትእዛዞች መፈፀማቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፡፡

33.በፍርድ ቤት የሚወሰኑ የወንጀል ቅጣቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ያደራጃል ወይም መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፡፡

34.የሞት ቅጣት ውሳኔዎችን ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ በኩል እንዲቀርብ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

35.በክልል የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ እና የክልል መንግስት መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ ይከራከራል ያስከብራል፣ እንዲከበሩ ያደርጋል፣ የሚከበሩበትን ሂደት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

36.የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶችን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ይመሰርታል፤ እንደአስፈላጊነቱ ተቋማትን ተክቶ በተናጠል ወይም በጋራ ይከራከራል፡፡

37.በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ያልተግባቡባቸው እና በግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች መካከል

yekkeero yoote mine woy yoote mini gobbaanni noo doorshu yekkeero tirate doogonni gumulantanno gede gumulote hedo aanno, araarunni gooffanno gede wo’naalsha assanno.

38. Meenxoonni mootimmate woxe roorreenyu noosi yoo mine qaxxaro shiqishe higanno gede assanno.

39. Muishu jaddo guma ikkkitinota yoote harinsho aana noo jiro gashshanno, ragirantanno gede gumulantino jiro hajo la’annonsa mootimmate bisubbara sayisanno.

40. Fitaabeerete qaxxaro shiqishirate woxu wolqa afidhinokki qaansooti baxxino garinni meyaata, qaaqquullenna geedhino manna riqiwe yekkeeramanno.

41. Woxu wolqa noonsakki jaddote gawajjno iillitinonsa miicamaano fiicantanno gede, heeshshonsa wirro tanta’nitanno gede hattono gawajjote ledo amadantino fitaabeerete horonsa agarsiisate insa riqiwe fitaabeerete qaxxaro shiqishanno, woy torbanno.

42. Qoqqowu mootimma hundaanni fultanno seerubba safote looso loosanno, mootimmate bisubbanni qixxaabbanno safote seerubba federaaletenna qoqqowu Bayriidi Seerinna wole seerubba ledo

የሚከሰቱ የፍትሐብሔር ክርክሮች በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጭ ባለ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገድ እንዲወሰን ውሳኔ ሀሳብ ይሰጣል በድርድር እንዲያልቁ ጥረት ያደርጋል፡፡

38.የተመዘበረ የመንግስት ገንዘብ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ያስመልሳል፡፡

39.የሙስና ወንጀል ዉጤት የሆኑት እና በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶችን ያስተዳድራል እንዲወረስ ዉሳኔ የተሰጠባቸዉን ንብረቶች ለሚመለከተዉ የመንግስት አካል ያስተላልፋል፡፡

40.የፍትሐብሔር ክስ ለመመሥረት የገንዘብ አቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችን፣ ሕፃናትን አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ወክሎ ይከራከራል፡፡

41.የገንዘብ አቅም የሌላቸው የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ተበዳዩች እንዲካሱ መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲሁም ከጉዳቱ የተያያዙ የፍትሐብሔር ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እነሱን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ያቀርባል ወይም ይደራደራል፡፡

42.በክልል መንግሥት የሚወጡ ሕጎች የሕግ ረቂቅ ዝግጅት ስራ ይሰራል፤

fiixoontinota ikkase buuxanno.

43. Qoqqowu seerubba qucu’mi asse loosatenna mittowa gamba asse injeessate looso loosanno; hajo la’annonsa bisubba ledo ikke federaalete seerubba Sidaamu Afiira tiranno.

44. Seeru allalaanora sufaminohanna harancho qajeelsha aanno, uyinanni gede assanno.

45. Qoqqowu dagoomira babbaxxitino doogonni seeru baqqeenyi roso aanno.

46. Qoqqowu yoote minna giddo yekkeerantanno ayyaayyamaanora fajjo aanno; haaroonsanno; loosonsa illaallisanno, ayyaayyamaanote disippiliinete hajo la’e gumulanno; fajjo seeru garinni feyaanno.

47. Qoqqowu giddo millissanno Tophiyu Danchumma Assate Uurrinshanna Maamarra borreessanno; seeru mannoomitte buuxisanno naqqasote woraqata aanno; loosonsa illaallissanno; buuxanno; seeru garinni borreessamansa feyaanno.

የመንግስት አካላት የሚያዘጋጁት ረቂቅ ህግ ከፌዴራልና ከክልሉ ሕገ መንግስትና ከሌሎች ሕጎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

43. የክልሉን ህጎች የኮዲፊኬሽንና የኮምፓይሌሽን ሥራ ያከናውናል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የፌዴራል ህጎችን ወደ ሲዳሙ አፎ ይተረጉማል፡፡

44. ዓቃቤያነ ሕግ ተከታታይ እና አጫጭር ሥልጠና ይሰጣል፤ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡

45. ለክልሉ ህብረተሰብ በተለያዩ ዜደዎች የንቃተ ህግ ትምህርት ይሰጣል፡፡

46. በክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሚከራከሩ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል ያድሳል፤ ስራቸውን ይቆጣጠራል የጠበቆችን ዲሲፕሊን ጉዳዮች አይቶ ይወስናል፤ በህግ መሰረት ይሰርዛል፡፡

47. በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን ይመዘግባል የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ስራቸውን ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣ በሕግ መሰረት ይሰርዛል፡፡

48. Hajote ledo xaadooshshu noosi seeri garinni taje borreessanno; buuxanno; kayisanno, feyaanno.

49. Qoqqowu giddo baatooshshiweelo uyinanni seeru irko dhaabbachishshanno hayyo qixxeesse handaaraho loossanno bisubba qineessanno; jeefishsha harunsanno.

50. Gobboomu mannihiimmate qoosso assootu loosu mixo kaima assatenni qoqqowunnita mannihiimmate qoosso assootu loosu mixo hajo la'annonsa bisubba ledo halamatenni qixxeessanno, jeefishshano harunsanno.

51. Seeru allalaanonni aamantanno gumulo seeru garinni aamamansa buuxanno illaallishshu gola uurrisanno; xee'ne xiinxallotenni badanno; xiinxallote gumi garinni taashshite qaafo assanno.

52. Seeru allaalaanoranna loosaasinete lo'oshu, ikkadimanna ogimma sufinonna deeru deerunkunni kaajijishate qajeelisha uytanno, gajeelshunna rosu kaayyo uynanni gede assanno.

53. Federaalete mootimmanni fajjo adhite qoqqowu giddo loossanno maammaranna mootimmaweelo uurrinshubba qorqortanno, hajo la'anonsa bissara ripoorte assitanno.

48. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሰነዶችን ይመዘግባል፣ ያረጋግጣል፣ ይሸራል፣ ይሰርዛል፡፡

49. የክልሉን ነፃ የሕግ ድጋፍ አሰጣጥ ስትራቴጂዎችን ቀርጾ በመስኩ የሚሰማሩ አካላትን ያስተባብራል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

50. ብሔራዊ የሰብአዊ መብት ድርጊት መርሀግብር መነሻ በማድረግ ክልላዊ ሰብአዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጃል አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

51. በዓቃቤያነ ሕግ የሚሰጡ ውሳኔዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን የሚያረጋግጥ የኢንስፔክሽን ክፍል ያደራጃል፣ ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ ይለያል፣ በግኝቱ መሠረትም እንዲታረሙ ያደርጋል፡፡

52. የዐቃቤያን ሕግ እና የሠራተኞችን አመለካከት፣ ችሎታና ሙያ በተከታታይና በየደረጃው ለማጠናከር ሥልጠና ይሰጣል፣ ሥልጠናና የትምህርት ዕድል እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

53. ከፌዴራል መንግስት ፈቃድ ወስደው በክልሉ ውስጥ የሚሰሩ ማህበራትን እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይቆጣጠራል፣ ለሚመለከተው አካል

54. Taakisete Kado Maccishitanno Komishiineta xaphooma loosu millimmo aliidimatenni massaganno, ha’runsitanno.

55. Qoqqowu Seeri Seejjote Minna Gashshooti Komishiine looso aliidimmatenni massaganno; harunsanno; qineessanno; seeru seejjamaano maaro afidhanno amanyoote diriirsanno.

56. Wolu seerinni uynonni ledote biillonyenna loosu qeecha jeefissanno; jeefisiisanno.

**GAFA SASE**

**LOOSU MINI TANTANO, BIILLOONYENNA GASHSHOOTE LAINOHUNNI**

8. **Loosu Mini Tantano**

Loosu mini aante noo tantanno heedhanosi.

1. Mittu Qaru Xaphphoomu Seeru Allalaanchinna Layinki Seeru Allalaanno;
2. Addi Addi Loosu Handaarra;
3. Massagooshshu Komite;
4. Qoqqowu Xaphoomu Seeru Allaalaano Gashshooti Qara Songo;

ሪፖርት ያደርጋል፡፡

54.የታክስ ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴን በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፡፡

55.የክልሉን ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤ የህግ ታራሚዎች ይቅርታ የሚያገኙበትን ስርዓት ይዘረጋል፡፡

56.በሌላ ሕግ የተሰጡ ተጨማሪ ሥልጣንና ተግባራትን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**የመሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት፣ ሹመት እና አስተዳደር**

8. **የመሥሪያ ቤቱ አደረጃጀት**

መሥሪያ ቤቱ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡፡

1. አንድ ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤያነ ሕግ፤
2. የሥራ ዘርፎች፤
3. የማኔጅመንት ኮሚቴ፤
4. የክልል ዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ፤

5. Seeru Allaalaano Galtino Wodho garini motoonsinanni seeru allaalaanonna hasiissanno loosaasine heerannosi.

9. **Biiloo'ma La'inohunni**

1. Qaru Xaphoomu Seeru Allaalaanchi Qoqqowu Pirezidaantichi shiqisheenna Amaalete Mine mootoo'manno.

2. Layinki Seeru Allalaanchi Qoqqowu Pirezidaantichinni mootoo'manno.

3. Taqu taqunkunni heedhanno seeru allaalshi loosu minna sooreeyye biiloonsate qaru xaphoomu seeru allaalaanchi maahoyye heera hasiissanno.

4. Aye deerrirano mootoonsinanni seeru allaalaanchi loosu mini soreessi afamooshshe afidhino uurrinshanni seeru rosinni maassaminoha ikka noosi.

10. **Biilloonyunni Ka'a Lainohuni**

Qaru xaphoomu seeru allaalaanchinna layinki xaphoomu seeru allaalaanchi hattono deerru deerrunni worranni seeru allaalshi sooreeyye biilloonyunni ka'ara dandiitanno.

5. በዓቃቤ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚሾሙ ዓቃቢያነ ሕግ፤ እና አስፈላጊ ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

9. **ስለሹመት**

1. ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ በርዕሰ መስተዳድሩ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማል፡፡

2. ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሾማል፡፡

3. በየእርከኑ የሚሾሙ የዓቃቤ ህግ መ/ቤት ኃላፊዎች ለሹመታቸዉ የዋና ጠቅላይ ህግ ይሁንታ ማግኘት አለባቸዉ፡፡

4. በየትኛውም ደረጃ የሚሾም የዓቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ሀላፊ በህግ ትምህርት እውቅና ካለው ተቋም የተመረቀ መሆን አለበት፡፡

10. **ከሹመት ስለመነሳት**

ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ እና ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እንደዚሁም በየእርከኑ የሚገኙ የዐቃቤ ሕግ ሀላፊዎች ከሹመታቸዉ ሊነሱ ይችላሉ፡፡

11. **Qara Xaphoomu Seeru Allaalaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1. Qaru xaphoomu seeru allalaanchi kaabinete miila ikke ogimmatenninna seeru garinni xaphoomu seeru allaalsha massaganno, gashshanno.

2. Konni quwira cinaancho quwa (1) aana worroonnihu noowa hee'reenna qaru xaphoomu seeru allaalaanchi konni woroonni noo biilloonyinna loosu qeechi heerannosi:

   a) Konni lallawi giddo quwa 7 hundaanni worroonni xaphoomu seeru allaalshi biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hosiisanno.

   b) Layinki xaphoomu seeru Allaalaanchinninna deerru deerrunku heedhanno seeru allaalaano loosu minna sooreeyye seeru allaalshi looso lainohunni uyitanno gumulo seera kaima assino garinni kaajjishanno, woyyeessanno, soorranno, kayisanno woy galagalcho la'antanno gede assanno.

   c) Seeru allaalaano wodho garini seeru allaalaano motoonsanno; wole kaa'lo

11.**የዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር**

1. ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የበላይ ኃላፊና የካቢኔ አባል በመሆን በሙያውና በሕግ መሠረት ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

   ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ሥር ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፡፡

   ለ) በምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እንዲሁም በየእርከኑ ባሉ የዓቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ኃላፊዎች የዓቃቤ ህግ ስራ አስመልክቶ የተሰጡ ውሳኔዎችን በሕግ ላይ በመመስረት ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይለውጣል፣ ይሽራል ወይም ጉዳዩ እንዲጣራ ወይም እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፡፡

   ሐ) ዓቃቢያነ ህግን በአቃቤያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ይሾማል

uyitanno loosaasine qoqqowu dagate owaante (siviliservisete) seeri garinni qaxaranno, gashshanno, seeru garinni geegiissanno.

d) Xaphoomu seeru allaalshi Istiraateejike mixonna baajeete qixxeessanno, fajjiniro loosu aana hosiisanno.

e) Xaphoomu seeru allaalshi loosu minira fajjinoonni baajeetenna loosu pirogiraame garinni fulo assanno.

f) Sayikki bisubba ledo assinanni xaadooshshira xaphoomu seeru allaalsha riqiwanno.

g) Xaphoomu seeru allaalaashi loosu jeefishshanna shallagote rippoorte qixxeesse mootimmate shiqishanno.

h) Loosu isilanchimmanna guma afiranno garinni biilloonyisinna loosu qeechisi aaninni gama booce layinki xaphoomu seeru allaalaanchira, seeru allaalaanoranna wole losaasinera aara dandaanno.

i) Loosu minira seerunni uynonni biillonyenna

ሌሎች ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ በህግ መሰረት ያሰናብታል፡፡

መ) የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ስትራቴጂክ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ሠ) ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በተፈቀደለት በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፡፡

ረ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደርጉት ግንኙነቶች ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን ይወክላል፤

ሰ) የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለመንግስት ያቀርባል፤

ሸ) ለሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነት በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለምክትል ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ፣ ዓቃቤያነ ሕግና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

ቀ) ለመስሪያ ቤቱ በሕግ የተሰጡ

loosu qeecha jeefisiisate loosu mini loosu tantano xiinxallo assateninna jeefisiisaanote amaale mininni kaajishiishatenni loosu tantano mannu wolqaninna lojestketenni wonshanno.

j) Seerunni uyinannisiha wole looso loosanno.

## 12. Layinki Xaphoomu Seeru Allaalaanchi Biilloonyenna Loosu Qeecha

Layinki xaphoomu seeru allaalaanchi galannohu qaru xaphoomu seeru allaalaanchi hundaanni ikke:

1. Qaru xaphoomu seeru allaalaanchira uyinoonni biilloonyenna loosu qeecha mixo mixiratenni, qiineesatenninna massagatenni qara xaphoomu seeru allaalaancho kaa'lanno.
2. Gamamaino handaara massaganno, gashshanno.
3. Qaru xaphoomu seeru allaalaanchi bande aannosiha loosu qeecha jeefisanno, jeefisiisanno.
4. Qaru xaphoomu seeru allaalaanchi heerannokki yannara riqiwo aa hoongiro balanxe biiloonsinoonni layinki xaphoomu seeru

ሥልጣንና ተግባራትን ለማሳካት የመስሪያ ቤቱን መዋቅር በማጥናትና በመስተዳደር ምክር ቤት በማጸደቅ መዋቅሩን በሰው ኃይልና በሎጀስቲክስ ያደራጃል፡፡

በ) በሕግ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 12. የምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር

ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ተጠሪነቱ ለዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ሆኖ፡-

1. ለዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉን ያግዛል፤
2. የሚመደብበትን ዘርፍ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
3. በዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
4. ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ በማይኖርበት ጊዜ ውክልና ያልተሰጠ እንደሆነ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የዋና ጠቅላይ ዓቃቤ

allaalaanchi qara xaphoomu seeru allaalaanchimma looso riqiwe loosanno.

13. **Seeru Allaalaano Gashshoote**

1. Qoqqowu seeru allaalaano qara xaphoomu seeru allaalaanchi shiqishonni seeru allaalaano gashshooti songonni billoo'mitannoha ikkanno.
2. Seeru Allaalaano galtanno gara Jeefisiisaanote Amaale Mini fushshanno wodhonni murranni.

14. **Seeru Allaalaano Biiloo'manna Gashshoote Lainohunni**

Seeru Allaalaano mootoomme qara sirnyuwa aante nooreeti:

1. Bayriidi Seeriranna Bayriidi Seeri amanyootira ammanama;
2. Seeru aliidimma ayirrisanno, ayirrisiisanno;
3. Halaalaanchimma;
4. Seerunni uyinoonni biilloonye calla ho'roonsira;
5. Mallaada hooga;
6. Suwashshimma;
7. Loosu fojo agara;

ሕግነት ሥራን ተክቶ ይሰራል::

13. **የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር**

1. የክልሉ ዓቃቤያነ ሕግ በዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ አቅራቢነት በዓቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባዔ የሚሾሙ ይሆናል፤
2. የዓቃቤያነ ሕግ አስተደደር አፈፃፀሙ የመስተዳደር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤

14. **የዓቃቤያነ ሕግ ሹመትና አስተዳደር መርሆች**

የዓቃቤያነ ሕግ ሹመት መሰረታዊ መርሆች የሚከተሉት ናቸው::

1. ለሕገ መንግስቱና ለሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱ ታማኝ መሆን፤
2. የሕግ የበላይነትን ማክበርና ማስከበር፤
3. ሀቀኝነት፤
4. በህጋዊ ሥልጣን መጠቀም፤
5. አለማዳላት፤
6. ቅንነት፤
7. የሥራ ሚስጥር መጠበቅ፤

8. Dancha akata afira;

9. Qoqqowunniha loosu afoo garunni coyra, maccisha, boorreessanna nabbawa dandaanoha,

10. Aye polotiku paarte miila ikkannokkihu.

15. **Seeru Allaalaano Gashshooti Qara Songo**

1. Seeru allaalaano gashshooti qara songo konni lallawinni uurritino.

2. Qaru xaphoomu seeru allaalaanchi songote gambisaancho ikkanno.

3. Seeru allalaanno gashshooti qara songora borrote mini, qaru xaphoomu seeru allaalaanchinni somamanno borrote mini sooreessinna loosoho hasiissanno wolootu seeru allaalaano heedhannosi.

4. Songote miilla, loosu amanynyootenna wole tittirote hajubba jeefisiisaanote amaale mini fushshanno wodhoni gumulantanno.

16. **Seeru Allaalaano Ogimmate Wolapho**

1. Xaphoomu seeru allaalshi loosu mini biilloonyesinna loosu qeechasi aye manchi woy

8. ጥሩ ሥነ-ምግባር ያለው፤

9. የክልሉን የሥራ ቋንቋ በአግባቡ መናገር፣ መስማት፣ መጻፍና ማንበብ የሚችል፤

10. የማንኛዉም ፖለቲካ ፓርቲ አባል የማይሆን::

15.**የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ**

1. የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2. የጉባኤው ሰብሳቢ ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ ይሆናል፤

3. የዓቃቤያነ ሕግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ የራሱ ጽህፈት ቤት፣ ለስራዉ የሚያስፈልጉ ዓቃቢያነ ህግ እና በዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ የሚሰየም የጽህፈት ቤት ኃላፊ ይኖረዋል፤

4. የጉባኤውን አባላት፣ የአሠራር ሥነ-ሥርዓትና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የመስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው የዓቃቢያነ ህግ አስተዳደር ደንብ ይወሰናል፡፡

16. **የዓቃቤያነ ሕግ የሙያ ነፃነት**

1. መሥሪያ ቤቱ ሥልጣንና ተግባሩን ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ጣልቃ

bisi hira eaanchimma nookkiha seeru garinni calla loosaanno.

2. Xaphoomu songo fushshitanno loosu biddissi noo gedeenni heereenna seeru allaalaano loosu qeechansa seeru garinni wolaphotenni gumultanno.
3. Xaphoomu seeru allaalaanchinni hanafe deerru deerrunkunni heedhanno seeru allaalaano konni lallawinni woy wolu seerinni garinni heerannonsa xa'mamooshshii noowa heereenna, seerunni uyinoonninsa loosu qeecha fulansanni iillitino gawajjora seeru xa'mamooshshi diheerannonsa.
4. Aye seeru allaalaanchi kotottote usursiissanno jaddo loosanna cirunkunni iilline amada hoongiro qaru xaphoomu seeru allaalaachi afikkinni amadamara woy usuramara didandaanno.

17. **Xa'mamooshshe**

Loosu jeefo aana xe'ne leellishino woy amanyootu huno loosino seeru allaalaanchi seerunni woy amanyootu wodhonni xa'mamannoha ikkanno. Tittirsha wodhotenni murranni.

**ገብነት ነፃ በመሆን በሕግ መሠረት ይፈፅማል፤**

2. **ጠቅላላ ጉባዔ የሚያወጣው የአሠራር መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓቃቤያነ ሕግ ተግባራቸውን በሕግ መሠረት በነፃነት ያከናውናሉ፤**
3. **ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና በየደረጃዉ ያሉ ዓቃቤያነ ሕግ በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ሕግ መሰረት ያለባቸው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሕግ መሠረት የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር በማከናወናቸው ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሕግ ተጠያቂነት የለባቸውም፤**
4. **ማንኛውም ዓቃቤ ሕግ በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ሲፈፅም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ እውቅና ሊያዝ ወይም ሊታሰር አይችልም።**

17. **ተጠያቂነት**

**በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ጉድለት ያሳየ ወይም የሥነ-ምግባር ጥፋት የፈጸመ ዓቃቤ ሕግ በህግ ወይም በሥነ-ምግባር ደንብ የሚጠየቅ ይሆናል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል።**

18. **Ku'laato Shiqishirate Qoosso**

1. Seeru allaalaanchi uyino gumulonni koffi yiino manchi deerru deerrunkunni noo seeru Allaalshi sooreeyyera ku'laato shiqishirate qoosso noosi.
2. Ku'laato shiqqino sooressino rahotenni buuxo asse gumulo aa noosi.
3. Ku'laato shiqqino sooressi hajo lede buuxate hasiriro ogeeyye amaddino komite uurrisa dandaanno.
4. Ku'laato buuxino sooreessi seeranna naqaashshete taje korkaatuwa kaima asse woriidi seeru allaalaanchi uyino gumulo kaajjishara, woyyeessara, soorrara, ki"ara woy hajo laino golira wirro la"anno gede qolara dandaanno.
5. Konni quwira cinaancho quwa 4 garinni uyinoonni gumulo aana koffeenyu noosi bisi deerra agare xaphoomu seeru allaalaanchi geeshsha shiqishira dandaanno. Ikkollana qaru xaphoomu seeru allaalaanchi gumulo goofimarchunnita ikkitanno.

19. **Qummeessa woy Laooshshu Hedo Shiqishate Qoosso**

1. Aye manchino xaphoomu seeru allaalaanchi

18. **አቤቱታ የማቅረብ መብት**

1. ዓቃቤ ሕግ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በየደረጃው ለሚገኙ የዓቃቤ ሕግ ኃላፊዎች አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፤
2. አቤቱታ የቀረበለት ኃላፊ ጉዳዩን በአፋጣኝ አጣርቶ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
3. አቤቱታ የቀረበለት ኃላፊ ጉዳዩን ለማጣራት አግባብ ያላቸውን ባለሙያዎች የሚያካትት ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡
4. አቤቱታውን የመረመረው ኃላፊ የሕግና የማስረጃ ምክንያቱን በመጥቀስ በበታች ዓቃቤ ሕግ የተሰጠውን ውሳኔ ለማጽደቅ፣ ለማሻሻል፣ ለመለወጥ፣ ለመሻር፣ ለማገድ ወይም ጉዳዩን አስቀድሞ አይቶ ወደ ወሰነው ክፍል ለመመለስ ይችላል፡፡
5. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 4 መሰረት በተሰጠዉ ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ አካል ቅሬታዉን ደረጃዉን ጠብቆ እስከ ዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ድረስ በየእርከኑ ላሉት የበላይ ሀላፊዎች ማቅረብ ይችላል፡፡ ሆኖም የዋና ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

19. **ጥቆማ ወይም አስተያየት የማቅረብ መብት**

1. ማንኛውም ሰው በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር ውስጥ የሚወድቅ

biilloonyinna loosu qeechi hundaanni heedhanno suwanna taala noose yee hedanno hajo woy loosantino yaannota akatunna see biddi yaa noose hajo woy amanyootunna seeru sa’o aye doogonni xaphoomu allaalaanchiranna deerru deerrunkunni noo seeru allaalaano sooreeyyera qummeessa woy laooshshu hedo shiqishara dandaanno.

2. Konni quwira cinaancho quwa 1 aana worronni garini qummeessa woy laooshshu hedo haadhanno bisubba qummeessa woy laooshshu hedubba ha’ne buunxanni harinsho hattono adhitanno qaafo dagate xawissanno amanyoote diriirsitanno.

**GAFA SHOOLE**

**ADDI ADDI WORO**

20. **Halamatenna Jeefisate Gadado**

1. Aye manchino konni lallawi giddo worroonni hajubba loosu aana hosiisate halamate gadadi noosi.
2. Aye poolisete miili seeru allaalaanchi seeru muro ayirrisatenna jeefisate gadadi noosi.

21. **Jaddote Xa’mamooshshe**

Wolu seerinni roore qorichishanoha ikka hoogiro:

ማንኛውም መታረምና መስተካከል አለበት የሚለውን ጉዳይ ወይም ተፈጽሟል የሚለውን የሥነ-ምግባርና የሕግ ጥሰት በማናቸውም መንገድ ለጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እንዲሁም በየአስተዳደር እርከኑ ላሉት የዓቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ኃላፊዎች ጥቆማ ወይም አስተያየት ለማቅረብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ ቁጥር አንድ መሰረት ጥቆማ ወይም አስተያየት የሚቀበሉ አካላት ጥቆማ አስተያየትና ቅሬታዎችን የሚቀበሉበትን የሚያጣሩበትንና የመፍትሄ እርምጃ የሚወሰድበት እና ለህብረተሰቡ የሚገለጽበትን የአሠራር ሥርዓቶች ይዘረጋል፡፡

**ክፍል አራት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

20. **የመተባበር እና የመፈጸም ግዴታ**

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተሸፈኑትን ጉዳዮች ሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የፖሊስ አባል የዓቃቤ ሕግን ህጋዊ ውሳኔ የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

21. **የወንጀል ተጠያቂነት**

በሌላ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ

1. Qoqqowu xaphoomu seeru allalaanchi woy seeru allaalaano loosonsa wolaphotenni loossannokki gede hira eannohu aye manchino mittu dirinni ajanokkinna onte diro rooranokki kototote usurinni qorichishamanno.
2. Qoqqowu xaphoomu seeru allalaanchi woy seeru allaalaano uyitanno seeru gumulo ayirrisannokkihu woy jeefisannokkihu hattono halamate gadado fulannokkihu aye manchino mittu dirinni roorannokki shotu usurinni woy 3,000 (sase kume) birra roorannokki woxu qorichinni qorichishamanno.
3. Seeru garinni seeru allaalaanchi uyino biddissa woy hajajo giwatenni dihajajameemmo yaano aye poolisete miili lamu dirinni roorannokki shotu usurinni woy 5,000 (onte kume) birra roorannokki woxu qorichinni qorichishamanno.

22. **Reekkote Woro**

1. Kuni lallawi loosu aana hosara albaanni konni lallawi giddo worroonni biilloonyenna loosu qeecha loossanni deerru deerrunkunni noo seeru allaalaano konni lallawi garini wolu deerrira gaamantannokki ikkiro albaanni loossanni keeshshitino taqinna deerrira loossanni suffannoha ikkanno.

በስተቀር፡-

1. የክልሉ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ወይም ዓቃቤያነ ሕግ ሥራቸውን በነፃነት እንዳያከናውኑ ጣልቃ የገባ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ወይም ዓቃቤያነ ሕግ የሚሰጡትን ህጋዊ ውሳኔ የማያከብር ወይም የማያስፈጽም እንዲሁም የመተባበር ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይ ከ 3,000 (ሦስት ሺህ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡
3. ሕጋዊ የሆነ የዐቃቤ ሕግ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ በመቃወም አልታዘዝ ያለ ማንኛውም የፖሊስ አባል ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ 5,000 (አምስት ሺህ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

22. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

1. ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በዚህ አዋጅ ላይ የተመለከቱት ስልጣን እና ተግባራትን ሲያከናወኑ የሚገኙ በየእርከኑ ያሉ አቃቤያነ ህግ በዚህ አዋጅ መሰረት ወደ ሌላ እርከን እስካልተመደቡ ድረስ በቀድሞው ሁኔታ በያሉበት እርከኑ

2. Kuni lallawi loosu aana hosasi albaani albiidi Wodiidi Daga Dagoominna Manni Qoqqowiranna albiidi Sidaamu Zoone seeru allaalshira aye deerrira la"antanni noo konni lallawi aana worroonni hajubba roorrenyinsa garinni uurritino seeru allaalshi loosu minnara higge la"antanno.

3. Xaadooshshu noonsa federaalete Amuraatunna Muishu Gargarooshshi Baxxino Amanyooti Seeri Kiiro 434/1997 (Woyyaawino lallawu kiiro 882/2007), Federaalete Amuuratunna Muishshu Gargarooshshi Komishiine Uurrisate Fulino Lallawi Kiiro 433/1997 (Woyyaawino lallawu kiiro 883/2007), hattono Muishshu Jaddo Murate Fulino Lallawu Kiiro 881/2007 qoqqowu giddo loosantanno Muishshu jaddubara loosu aana hosanno.

4. Daddalu Heewonna Dikkiraanote Agarooshshi Lallawi Kiiro 813/2006 hattono wole seerubba giddo Daddalu Heewonna Dikkiraanote Agarooshshi Biilloonyira uyinoonni seeru allaallshi biilloonyi qoqqowu seeru allaalshiha ikkanno.

23. **Baajeete Lainohunni**

Qoqqowu xaphoomu seeru allaalshi mootimmatenni gaammanni baajeetenni galanno.

የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

2. ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በነባሩ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በቀድሞዉ የሲዳማ ዞን በዓቃቤ ህግ እጅ በማንኛዉም ደረጃ ላይ የነበሩ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮች እንደየስልጣን እርከኑ ለተዋቀረ ዓቃቤ ህግ የሚተላለፍ ይሆናል፡፡

3. አግባብነት ያላቸው የፌደራል የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ አዋጅ 434/97 (በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለ)፣ የተሻሻለው የፌደራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 433/2007 (በአዋጅ ቁጥር 883/2007 እንደተሻሻለ)፣ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 881/2007 በክልሉ በሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች እንደየአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

4. በንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እንዲሁም በሌሎች ሕጎች ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን የተሰጠው የዓቃቤ ሕግነት ሥልጣን የክልል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መ/ቤት ይሆናል፡፡

23. **በጀት**

የክልል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ከመንግስት በሚመደብለት በጀት ይተዳደራል::

24. **Shallagote Taje Lainohunni**

1. Xaphoomu seeru allaalshi wo'manna halaalaancho shallagote taje amadanno.
2. Xaphoomu seeru allaalshi shallagotenna woxe la'anno tajubba qoqowu Qaru Qorqorshu woy Qaru Qorqorshinni somantanno qorqoraanonni diru dirunni qorqorsha assitanno.

25. **Wodhonna Biddissa Fushshate Biilloonye**

1. Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini konne lallawa loosu aana hosiisate wodho fushsha dandaanno.
2. Xaphoomu seeru allaalshi konne lallawanna konne quwa cinaancho quwa 1 garinni fultanno wodho loosu aana hosiisate biddissa fushshara dandanno.

26. **Jeefisantannokki Seerubba**

Konni lallawi ledo kibbamanno aye seerino konni lallawira worroonni hajubbara jeefamara didandaanno.

27. **Lallawu Loosu Aana Hosanno Yanna Lainohunni**

Kuni lallawi Qoqqowu Amaale Mine kajjino Ella 29, 2012 M.D. barrinni hanafe loosu aana hosanno.

24. **የሂሳብ መዛግብት**

1. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የተሟላና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልል ዋና ኦዲተር ወይም በዋና ኦዲተር የሚሰየሙ ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

25. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

1. የመስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀያ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

26. **ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚት አይኖራቸውም፡፡

27. **አዋጁ ስራ ላይ ስለመዋል**

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤት ከፀደቀበት ከዛሬ ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ ይዉላል፡፡

**Hawaasa, Ella 29, 2012 M.D**

**Desta Ledamo.**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma**

**Pirezidaanticha**

**ሀዋሳ፤ ሰኔ ፳፱ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳደር**